የዕለት ስንቅ

2ኛ መጽሐፍ

በመሐሪ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ

1999 ዓ.ም ታተመ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት
ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::

Copyright © Mehari Taddesse Wolde Giorgis

March 2005

All rights reserved.

አሳታሚና አከፋፋይ፣
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
የስልክ ቁጥር 011-349-3252፣ 011-551-2973
ፋክስ 251-1- 551-1242፣
ኢ-ሜይል:- simmedia@ethionet.et

ዋና አርታኢ:- ዘነበ ገብረሐና
አርማት:- ሰላመአብ አሰፋ እና ዮዲት ኃይሉ
የኮምፒውተር ስቀማ:- ጥሩወርቅ በቀለ
የገጽ አቀማመጥ:- ዓለምፀሐይ እውነቱ
የሽፋን ሥዕል ዝግጅት:- ሮቤል ተስፋዬ

Printed by SIM Press

ማውጫ

የአሳታሚው ማስታወሻ.....
1. አሾህን በአሾህ.....7
2. የደፈጣ ውጊያ.....9
3. አዲስ ጅማሬ.....11
4. ቀስተ ደመና.....13
5. «ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም».....15
6. ቃል ኪዳን.....17
7. «በሰፈሩት ቁና...».....19
8. በክርስቶስ አሸናፊ ከሆንን፣ መንፈሳዊ ውጊያ ትርጉሙ ምንድን ነው?.....21
9. ከንቱ ሩጫ.....23
10. የጦሳ ተራራ.....25
11. የትራፊክ ቅጣት.....27
12. እግዚአብሔርን መፍራት ዘመንን ታረዝማለች.....29
13. «አሚሚቴን አሳምርልኝ».....31
14. ኢዮርብዓም - የትውልድ ነቀርሳ.....33
15. እናት ወልዳለች.....35
16. «ተንጋልለው ቢተፉ...».....37
17. ቅብብሎሽ.....39
18. «ለበጎ ነው».....41
19. ናፍቆት.....43
20. 5 + 4 = አንድ ብር ከስሙኒ.....44
21. «ትልቅ መርከብ».....46
22. አርጥብ ሲሚንቶ.....48
23. አንጐሉን መረመሩት.....50
24. «በኃጢአት የተገኘ መዝገብ ጥቅም የለውም».....52
25. «ደፍሮ የሚገሥጸ ግን ሰላምን ያደርጋል».....54
26. «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው. . .».....55
27. አቤልና ቃየን.....57
28. ወንጌል - ኢየሱስ ያድናል ማለት ብቻ አይደለም!.....59
29. ጋሽ ጨንዳ.....61
30. አመድ በዱቄት ይስቃል.....63

31. የቀልድ አምልኮ 65
32. የጠላት ክልል 67
33. ሆድ ምታት 69
34. የሚያባርር ኑሮ 71
35. ቃል ኪዳን 73
36. ኤልሻዳይ 75
37. አሲምሌሽን 77
38. የቁራ ግማት 79
39. የጳውሎስ ኾኖ ሥዕሎች 81
40. አርብ የሳቀ እሑድ ያለቅሳል 83
41. የውሻ ዋና 84
42. ሚዛን 1 86
43. ሚዛን 2 88
44. ሚዛን 3 90
45. ሚዛን 4 92
46. ሚዛን 5 93
47. ሚዛን 6 95
48. ሚዛን 7 97
49. ሚዛን 8 99
50. አክሱም 101
51. ላሊበላ 103
52. ምርቃት 105
53. «ከመጥፎ ጓደኛ...» 107
54. ሞባይል ሊመጣ ነው 109
55. ለምን እፈራለሁ? 111

የአሳታሚው ማስታወሻ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ባዘጋጀው አማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ «ስንቅ» የሚለው ቃል «ለጉዞ ወይም ለመንገድ የተዘጋጀ ምግብ» ተብሎ ፍቺ ተሰጥቶታል። እኛ ክርስቲያኖች በምድር ሳለን ተጓዥ መንገደኞች እንደሆንን እና አገራችን/ ቤታችን በሰማይ እንደ ሆነ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ በግልጽ ሰፍሯል። እንደ መንገደኝነታችን ደግሞ ለጉዞ የሚሆን ስንቅ/ምግብ ያስፈልገናል። ምግባችንን የምንመገበው በየዕለቱ ሲሆን፣ አብዛኞቻችን በቀን ውስጥ ቢያንስ ሦስቴ ምግብ እንጎርሳለን። መንፈሳዊውንም ምግብ እንዲሁ አዘውትረን መመገብ ይኖርብናል። አለበለዚያ ግን መንፈሳዊ ሕይወታችን ከሲታ፣ እንዲሁም ፍሬ አልባ እና የሐሰት ትምህርትን ፈተና ማሸነፍ/ መቋቋም የሚሳነው ይሆናል።

የዘመኑ የኑሮ ዘይቤ አዝማሚያ ሲመለከቱት ብዙ ነገር «ፈጣን» ወይም «instant» እየሆነ የሚሄድ እና ፉክክር/ውድድር የበዛበት ይመስላል። ስለዚህም በውድድሩ ለማሸነፍ ያለን ፍላጐት አብዛኞቻችንን «ሯጮች» አድርጎናል። ወፍ ከጮኸበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ውድቅት ሌሊት ድረስ በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ከአንዱ ጉዳይ ወይም ተግባር ወደ ሌላኛው በሚያሽከረክረን የድርጊት መዘውር ስንሾር እንውልና እናመሻለን። በዚህ ሁሉ መሐል የሥጋዊ ምግባችንን ጉዳይ ለአፍታም እንኳ ቸል ሳንል፣ መንፈሳዊ ምግባችንን ግን ወይ እንደ ነገሩ አድርገን እንይዘዋለን፣ አለያም አንገዋልለን፣ ማከናወን ከሚገባን ጉዳዮች ዝርዝር ውስጥ የመጨረሻውን ረድፍ እናስይዘዋለን፣ ከዚያም በድካምና በዝለት የዕለቱን እንጥፍጣፊዋን ጊዜያችንን እንሰጠዋለን፣ ብዙ ጊዜ ደግሞ «በአቡነ ዘበሰማያት» የጀመርነውን ዕለት ለመሸኘት፣ «በሰላም ያዋልከኝ፣ በሰላም አሳድረኝ» ብለን ወደ መኝታችን እንሄዳለን።

እንግዲህ እንዲህ ባለ ሁኔታ ላለነው ለዚህ ዘመን ክርስቲያኖች የዕለት ስንቅን የመሰለ እጥር ምጥን ያሉ፣ ነገር ግን ኃይለኛ መልእክት ያላቸው ጽሑፎች በአንድ ጥራዝ መቅረባቸው ጥቅማቸው የትየለሌ ነው። ወንድማችን መሐሪ ታደሰ አንደኛውን

መጽሐፍ በ1995 ዓ.ም ካበረከተልን በኋላ፣ አሁንም እንደ ገና ጠቀሜታውን በእጅጉ ስለሚያምንበት ይኸው እነሆ በቀጣይ ገጾች የሰፈሩትን መልእክቶቹን ለእግዚአብሔር ክብርና ለእኛ ለወገኖቹ ጥቅም ይሆኑ ዘንድ አበርክቶልናል።

ላለፉት 65 ዓመታት በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ረገድ ሕዝበ ክርስቲያኑን በታማኝነት ሲያገለግል የቆየው የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ዛሬም በተጠናከረ መልኩ አገልግሎቱን በመቀጠል፣ ከትርጉም ሥራዎች በተጨማሪ አገራዊ ሥራዎችን ማበረታታቱን ቀጥሏል። በዚሁ መሠረት፣ የመሐሪን 2ኛ መጽሐፍ የቅድመ-ጎትመት መሰናዶ አጠናቅቀን እና አሳትመን አሁን በእጃችሁ ባለበት መልኩ አቅርበንላችኋልና በሚገባ ተጠቀሙበት ብለን በታላቅ አክብሮት እንጋብዛችኋለን።

መልካም ንባብ! መልካም ጥሞና! ጌታን አክባሪና አስከባሪ ሕይወት ይሁንላችሁ!

ዘነበ ገብረሐና
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ
ዝግጅትና ስርጭት ሥራ አስኪያጅ

እሾህን በእሾህ

እሾህ ጫፉ ሹል ነው። ያለ ጫማ በባዶ እግር የሚጓዘውን ድሃ ወገኔን ዘወትር ያሠቃየዋል። ወይ ከተረከዙ አለያም መሃል እግር ላይ እየተሰካ ያሳቅቀዋል። እሾህ መድኃኒትም ነው። እግራችንን ወግቶ ለተሰወረ የእሾህ ቁራጭ መርፌ ወይም መርፌ ቁልፍ የሌለው ሰው ሌላ ሾል ያለ አጋም እሾህ ፈልጉ ገላውን በጥንቃቄ እየዘነጣጠለ ራሱ በራሱ ላይ «ቀዶ ምንገላ» ያካሂዳል። እሾህ የእንጨት ለቃሚዎች ጠላትም ወዳጅም ነው። ሲያሻው ያስለቅሳቸዋል፣ በል ሲለው ደግሞ ያሳርፋቸዋል።

ነገሬን በእሾህ የጀመርኩት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ትዝ ብሎኝ ነው። ያው የሕያዋን ሰዎች እናትና አባት የነበሩት አዳምና ሔዋን ሕግ ተላልፈው ምድር ተረገመች። አዳምንና ሔዋንን ለምን ኬላ እንደ ጣሱ ጠይቆ ካዳመጣቸው በኋላ በቀጥታ እባቡን ፍርድ ፈረደበት እንጂ እንደ ሰው ልጆች የጥፋቱን ምክንያት አልጠየቀውም። በመቀጠልም አዳምን እንዲህ አለው፤ «ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፣ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ።» (ዘፍጥረት 3:17-18) አዳም ፍርዱን ሰምቶ መውጫውን ደግሞ ለእግዚአብሔር ትቶ ኑሮን ተጋፈጠ እንጂ እሳት የላሰ ጠበቃ ገዝቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሊከራከር አልፈለገም።

ወደ ራሳችን ሕይወት መለስ ብለን ኑሮአችንን ስንፈትሽ ብዙ ጊዜ ለምናጠፋው ጥፋት ሰበብ ፈልገን ከፍርድና ወቀሳ ለመዳን ዙሪያ ጥምጥም እንዞራለን። እስኪ ቆም ብላችሁ አንድ ሁለት ወይም ሦስት አጋጣሚዎቻችሁን መለስ ብላችሁ አስታውሱ። ማጥፋታችሁን እያወቃችሁ፣ እግዚአብሔርም እንዳዘነ ገብታችሁ በንስሐ ፋንታ ሌላ አማራጭ ያሻችሁበት ነገር ምን ነበር? ከላይ «እሾህን በእሾህ» እንዳልኩት በአዳም ኃጢአት ምክንያት የመጣውና በእሾህ የተመሰለው መከራ፣ ያለመመቸትንና ሞትን ወግቶ በሚያሠቃየው ሳይሆን በሚነቅለው እሾህ መወገድ አለበትና እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆነ።

በመስቀልም ላይ ሲሞት በጨከነ ጊዜ የእሾህን አክሊል አምጥተው ካናቱ ላይ ደፉበት። የግንባሩንና የጭንቅላቱን ቆዳ ዘልቆ እየሰረሰረ የደም መተላለፊያዎቹን እየበሳ በጥዝጣዜ አሠቃየው። የአዳምን እሾህ ጌታ ኢየሱስ ነቀለው። ማቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ «ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፣ ከእሾህም አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ፣ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ፣ በፊቱም ተንበርክከው፡- የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤ ተፉበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት። ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት. . .» (ማቴ. 27:27-31)። ዛሬን ስንኖር ጌታን ስለዚህ ውለታው እናመሰግነው፣ ስለ እኛ ኃጢአት እርሱ ኃጢአት ሆኖ፣ እሾህን ነቅሎ ሰላምን ስለ ሰጠን ዳግመኛ ኃጢአት ላለማድረግ እንወስን። ጊዜ ወስደንም በዚህ ጉዳይ ላይ እንጸልይ።

<u>መዝሙር</u>፡- ቁስልህን አሳየኝ፣ ሥቃይህን አሳየኝ፣
መስቀልህን አሳየኝ፣ መከራህን አሳየኝ፣
ሥጋ ሥጋዬን ሳይ ጸጋህ እንዳይለየኝ።
ቁስልህን አሳየኝ . . .

የደፈጣ ውጊያ

ናይእግዚ ጎሩይ የተባለ ወጣት ጸሐፊ በአንድ ወቅት ስለ ሽሮ ወጥ በጻፈው መጣጥፍ ላይ፣ «ሽሮ ካለ ኢትዮጵያውያን አሉ፤ ኢትዮጵያውያን ካሉ ደግሞ ሽሮ አለ።» ብሎ ጽፏል። ሽሮ ስለምንወድ በዶኬ ጀመርኩ እንጂ መጻፍ የፈለግሁት ስለ ውጊያ ነው። ልክ እንደ ሽሮው የኢትዮጵያም ታሪክ በተለይ ደግሞ ከ1965 ዓ.ም እስከ አሁን ያለው ከረዛብና ከጦርነት ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ደግሞ ከልጅነታችን ጀምሮ የጦር መሣሪያ ምላጭ መሳብ እንድንማር አስገድዶናል። ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤ ምንም እንኳ ወታደር ሆኖ፣ ጦር ሜዳ ሄዶ ባይዋጋም፣ በየቤቱ ቢያንስ አንድ የጦር ሠራዊት አባል አይጠፋምና ስለ ውጊያ ስልት በወሬም ቢሆን ያውቃል።

ከውጊያ ስልቶች አንዱ የደፈጣ ውጊያ ነው። የጠላት ሠራዊት አገር ሰላም ነው ብሎ እየፎለለ ሲመጣ፣ ከአካባቢው ጋር ተመሳስለው አመቺ ቦታ ላይ ያደፈጡ ባላጋራ ወታደሮች ይጠብቁታል። ያደፈጠን አንድ የጠላት ወታደር ለመደምሰስ የሚመደበው የሰው ኃይል ሦስት ሲሆን፣ ያደፈጠው ሰው ደግሞ እንዲሁ ለሦስት ሰው በቂ ነው ተብሎ ይታመናል። አድፋጩ ከዙሪያ ገባው ጋር ስለሚመሳሰል ለመለየት አዳጋች ነው። የሚያዋጣው በብዙ ጥንቃቄ እይታን አስተካክሎ በእርጋታ መራመድ ነው። እንዲህ በማድረግ ቢያንስ ቢያንስ አፈስ አፈስ እያደረጉ በሚጓዙት ላይ ከሚደርሰው አደጋ መትረፍ ይቻላል።

ለዚህም ነው እግዚአብሔር ቃየንን ሲመክረው፣ «መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፣ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።» (ዘፍጥረት 4፡7) ያለው። ልብ ከሸፈተ እግር ይከተላል። እግር የሚረግጠውን ይመርጥ ዘንድ ዓይን ካላየለት፣ ልቦና ካልተመለከተለትና መንፈስ ካልመራው መጨረሻው ጥፋት ይሆናል። እግዚአብሔርም ለእኛ የሚናገረን ይህንኑ ነው። ከሁኔታዎች ጋር ተመሳስሎ ሕይወታችንን ሊነጥቅ የሚያደባ ኃጢአት ሸምቆብናልና ዕለታዊ ኑሮአችንን እየፈተሽን መልካምን ለማድረግ እንትጋ።

እግዚአብሔር የተናገረንን ትተን በራሳችን የምንጓዝ ከሆነ እንደ ቃየን ፈቃዳችንን እንፈጽማለን። ፍጻሜውም ጸጸትና መቅበዝበዝ ነው። ያደፈጠ ኃጢአት በቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት፣ በጐዳና ደግሞም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለና እንንገሥበት። በቶሎ የኃጢአት ምኞትን ሰብረን መልካም በማድረግ እንካደው። ካልሆነ ግን ወንድማችንን እናጠፋለን። መንፈሳዊ ሕይወታችንን በጥንቃቄና በፍርሃት እየተንከባከብን ኃጢአት ባለመሥራት በመታዘዝ ስልት እናሸንፈው። ኃጢአትን የምንረታው በሥጋ ብርታት ሳይሆን በጥበብ ነው። ይህ ጥበብ በክርስቶስ ኢየሱስ ዕለት ዕለት፣ በየሰዓቱ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣብቆ ትእዛዙን በመጠበቅ መኖር ነው። እስኪ ዛሬ ከጌታ ጋር ተጣብቀን ለመዋል ምን ማድረግ እንዳለብን አውቀን ቃሉን ለመኖር የምንችልበትን መንገድ እንፈልግ።

<u>መዝሙር፡-</u> ክርስቲያን ሆይ ንቃ ከሙታን ተነሣ፣
ጋሻ ጦርህን ያዝ ዓላማህን አንሣ።
ሥጋና ደም አይደል ውጊያው የመንፈስ ነው፣
አንተ ተነሥ እንጂ ድሉ የእግዚአብሔር ነው።

አዲስ ጅማሬ

«ልጅነት ተመልሶ አይመጣም» የሚልን መጽሐፍ አንብባችኋልን? የዚህን መጽሐፍ የውስጡን ነገር ትታችሁ ርእሱን ብቻ እንኳ ደጋግማችሁ ብታሰላስሉት የሚገርም እውነት አለው። አንዳንድ ጊዜ ልጅ መሆን አምሯችሁ አያውቅም? ዘመኔ እንደ ቴፕ ክር የኋልዮሽ ተጠንጥኖ እንደገና መኖር ብችል ኖሮ በከንቱ ያሳለፍኩትን ዕድሜዬን አስተካክዬ እኖረው ነበር። ግን ምን ዋጋ አለው! ወደ ኋላ ተቀልብሼ ያለፈውን ማቃናት አልችልም። ሆኖም ግን፣ አንድ ነገር የማድረግ ዕድል አለኝ። ይኸውም የዛሬንና የወደ ፊቱን በጥንቃቄና በጥበብ መኖር። ባለፈው እየተቆጨሁ፣ ነገን እየተመኘሁ፣ ዛሬን ከማበላሸው፤ ዛሬን እንደሚገባ መኖር ከቻልኩ ነገን ለመኖር ዋስትናዬ ይሆነኛል። ሰው ሆኖ የማይስት የለም። በፍጹም ቅንነት የምንሠራው ነገር እንኳ እንከን አያጣውም። ማድረግ የምንችለው ነገር ያለፈውን ትተን በአዲስ ጅማሬ መኖር ነው።

እግዚአብሔርም እኮ ነገር እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ፣ የጠማሚት ተጉዞበት ያውቃል። ከላይ ያልኩትን ከጠረጠራችሁ አሳቤን ቀጥዬ ላብራራ።

እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ ሁሉን አበጅቶ ኑር ቢለው፣ ተሳስቶ በእግዚአብሔር ፊት የነበረውን ዋጋውን ቀነሰ። አዳም ረከሰ። እንግዲህ ረከሰ ስንል ምን ማለታችን መሰላችሁ? የሚያማምሩ ዘመናዊ የቤት መኪናዎች በአንድ ብር አምስቱ ሲሸጡ እንደ ማለት ነው። ሽራቱን ሆቴል በ50 ሣንቲም ቢሸጥ። ኧረ ከዚያም የባሰ ነው የአዳም መርከስ!! አዳምን ያመመው የኃጢአት በሽታ ወደ ልጁ ቃየን፣ ከዚያም ወደ ጎብረተሰቡ ተጋባ። ዓለም በኃጢአት ተጥለቀለቀ። ታዲያ እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንደዚህ በኃጢአት ይተራመስ ዘንድ መሻቱ ነውን? በፍጹም አይደለም። ነገር ግን ሰው በራሱ ፈቃድ ጠምዝዞ ባልተገባው መንገድ ፈረጠጠ።

ይህን ጊዜ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በጥፋት ውኃ አጥፍቶ በኖኅ አዲስ ጅማሬን ጀመረ (ዘፍጥ. 6)። በድጋሚም ሰዎች

በክፋታቸው ሲገፉ፣ በአብርሃም አዲስ ጅማሬን ጀመረ (ዘፍጥ. 12)። እግዚአብሔር የሰውን ዘር በውኃ አጥፍቶ በኖኅና በቤተሰቡ አዲስ ጅማሬን ከጀመረ፣ እኛማ እንዴታ! ያሉንን ጥቂት መንፈሳዊ ነገሮች ይዘን የቀረውን ውጥንቅጥ ሕይወታችንን በደሙ ጐርፍ ብናጥብና ባሉን መልካም ነገሮች አዲስ ጅማሬ ብንጀምር ብዙ እናተርፋለን። እስኪ ዛሬ ቆም ብላችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቅንነት ራሳችሁን ጠይቁ፡- ክርስቲያን ከሆንኩ ምን አለማሁ? ምንስ አጠፋሁ? ያለፈውን ላለመድገም ምን ላድርግ? በሕይወቴ የሚገለጡ የመንፈስ ፍሬዎች ምን ምን ናቸው? እነርሱን ጠብቄ ለእግዚአብሔር የማይመቸውን ነገሬን እንዴት ላስወግደው? ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ዛሬ ምን ማድረግ እችላለሁ?

<u>መዝሙር</u>፡- ያለፈው በደሌን ተወው፣

ጌታዬ አደራ አታስታውሰው፤

እባክህ ዕድል ስጠኝና

ልጅህ አድርገኝ እንደገና።

ቀስተ ደመና

እኔ ሁልጊዜ የሚደንቀኝ የእስራኤልና የአረቦች ስምምነት ነው። በየጊዜው ጦርነትን ለማቆም ቢዋዋሉም፣ ፊርማው ሳይደርቅ መልሰው ጦርነት ይጀምራሉ። ሽክርክሮሹ እንዲሁ እንደ ተንከባለለ ይሽው እስከ ዛሬ ደርሷል፣ በየቀኑም ሰው ይሞታል። አሜሪካም አሁን ለጊዜው ኃያል አገር ሆናለችና ከጠቀማት ትስማማለች፣ ካልሆነ ደግሞ ቃል ኪዳኗን ለማፍረስ ወደ ኋላ አትልም። ከመንግሥታት ጀምሮ እስከ ተራው ሰው ድረስ ቃልን ማጠፍና አባይ መሆን እንደ ብልጥነት ይታያል። ዛሬ የገባውን ቃል ነገ ይሸመጥጣል። ዛሬ የገነባውን ነገ ያፈርሳልና። ከዚህ የተነሣ መተማመን ጠፍቶ፣ ሁሉም የጉሪጥ ይተያያል። በወረቀት የተፈጸመ ውል እንኳን ሳይቀር ፍሬ ቢስ ሆኗል። ሰውም ፍርድ ቤት እንዳይሄድ ነገር መጓተቱን ጥላቻ እንዲያው እህህ እንዳለ ይኖራል።

ምንም እንኳ የምንኖረው ታማኝነትን የሚያጐድሉ ሰዎች በበዙበት ዓለም ቢሆንም፣ እንደ ከዋክብት ደምቀው አልፎ አልፎ የሚገኙ ታማኝ ሰዎች አይጠፉም። እንደ እነዚህ ጥቂት ቅዱሳን በረከሰ ትውልድ መካከል ራሱን ለእግዚአብሔር አስገዝቶ የኖረ አንድ ሰው ነበር። እርሱ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር እርሱን ለዘር አስቀርቶ በቃል ኪዳንም በእርሱ በኩል ከዓለም ጋር ተዛምዶ ፍቅሩን ይገልጥ ዘንድ ምክንያት ሆኗል። ታሪኩ የሚገኘው በዘፍጥረት ምዕራፍ 6-10 ሲሆን፣ እኛ ዛሬ የምንዳስሰው ግን ምዕራፍ 9፡8-12 ያለውን ነው። እንዲህ ይላል፡-

> «እግዚአብሔርም ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- እኔም እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ፤ ከእናንተ ጋር ላሉትም ሕያው ነፍስ ላላቸው ሁሉ፣ ከእናንተ ጋር ከመርከብ ለወጡት ለወፎች፣ ለእንስሳትም ለምድር አራዊትም ሁሉ፣ ለማንኛውም ለምድር አራዊት ሁሉ ይሆናል። ቃል ኪዳኔንም ለእናንተ አቆማለሁ፤ ሥጋ ያለውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም፤ ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም።»

ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ በነበረ ጊዜ ጌታ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በጥፋት ውኃ የሰውን ዘር አጥፍቶ እንደገና ከኖኅ ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን ከራራ፣ በቃሉ ታማኝ ነውና ልናመሰግነው ይገባል። ሆኖም ግን፣ በኃጢአተኞች ላይ መጨከኑንም አንዘንጋ። ዛሬም በኃጢአት የምንኖር ካለን በቶሎ እንመለስ። ምድር በውኃ ሳይሆን በእሳት መጥፋቷ አይቀርምና እግዚአብሔርን በመምሰል እንትጋ። ቀስተ ደመና ባየን ቁጥር እግዚአብሔርን ስለ ቃል ኪዳኑ እናመሰግነው። በውሏችን ሳናውቅ የሳትንብት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እንዲገሥጸን እንጸልይ።

<u>መዝሙር</u>፦ እንደ ኖኅ እንደ ሎጥ ዘመን፣
ኃጢአትን እጅግ አበዛን።
ጌታ ሆይ እባክህ ገሥጸን፣
አባት ነህና ቆንጥጠን፣
ስንጠፋ ዝም አትበለን። (2)

«ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም»

በኢህአፓ ዘመን፣ «ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም» የሚል የፖለቲካ መዝሙር ይዘምሩ ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ። ግን እኮ እውነታቸውን ነው። የቆሙለት ነገር እውነት ከሆነና በሕዝቡ ዘንድ ሰርጾ ተቀባይነትን ካገኘ፣ ትግሉ ርቆ ይጓዛል። ካልሆነ ግን፣ ትግሉ ይጨነግፍና ሕይወት አልባ ይሆናል።

እግዚአብሔር የሚናገረውን የሚያውቅ፣ የተናገረውንም የሚፈጽም አምላክ ነው። እስኪ ይታያችሁ፣ አምላክ ዝቅ ብሎ አብርሃምን ከሚኖርበት አገር ሲያወጣው። ለመሆኑ አብርሃም እግዚአብሔርን ምኑን አምኖ ተከተለው? መልሱ <ቃል> ተቀብሎ ነው የሚል ይሆናል። አብርሃም የሄደው፣ ከማይመች ስፍራ ወይም ከገጠር ወደ ከተማ አይደለም። የቁጣዘው ከከተማ ማለትም በጊዜው በሥልጣኔዋ ከበለጸገች አገር ተነሥቶ ምንም ወደማይታይበት በረሃ ነው የተጓዘው። አብርሃምም ከወጣ በኋላ ሌላ የተስፋ ቃል ደግሞ ተሰጠው። የተስፋውን ፍጻሜ ቢጠብቅ ቢጠብቅ አልደርስ አለ። ጭራሹኑ ተስፋው እየደበዘዘ፣ ደቂቃ ቆጣሪዋም እየተሸከረከረች፣ ቀናት ቀንና ሌሊትን እያፈራረቁ አስረጁት።

ሥጋዊ ነገሩ እየተሟላ በከበት ብዛት ቢባረክም፣ በየዕለቱ የሚራቡትን ከብቶች እያየ የእርሱ ዘር ያለማፍራት ነገር ራስ ምታት ሆነበት። አንድ ቀን በዘፍጥረት ምዕራፍ 15 ላይ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ «እኔ ጋሻህ ነኝ» ቢለው፣ አብርሃምም መልሶ በዙሪያው የነበሩትን መረጃዎች በመጠቀም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መፈጸሚያ እንደ ራቀው ለአምላኩ ድካሙን ገለጠ። እግዚአብሔርም ከዋክብትን እያሳየ ዘሩም እንደዚሁ እንደሚበዛ ሲነግረው፣ «አብርሃም አመነ» ይላል።

ዘፍጥረትና ሮሜ ምዕራፍ አራት፣ አብርሃምን የእምነት ሰው እያሉ ቢደግፉትም፣ እርሱ ግን ምድሪቱን ይወርስ ዘንድ እንዳለው በድጋሚ እግዚአብሔር ሲያስረግጥለት፣ «በምን አውቃለሁ?» ብሎ በውስጡ የሚያስተጋባውን ጥርጣሬ አፈነዳው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። በተከፈሉ የእንስሳት ብልቶች መሃል ብቻውን «በምድጃ ጢስ» ተመስሎ፣

«ብከዳህ፣ እንዲህ ይክፈለኝ» በማለት አልፎ ለዘላለም ላይጥለው ቃል ኪዳን ገባለት።

አብርሃም ቢያልፍም ይስሐቅ ተተክቷል፣ የተስፋ ቃሉም ተፈጽሟል። እግዚአብሔርም ከይስሐቅ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ ከዚያ ያዕቆብ ተተካና ዮሴፍን አስከተለ። ከዮሴፍ በኋላ ደግሞ ሙሴ ቀጠለና በኢያሱ ዘመን እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን የርስት ጉዳይ በመጽሐፈ ኢያሱ ሲፈጽም እናያለን።

ለአባቶቻችሁ፦ እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና፣» (ኢያሱ 1:6)። «እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ። ወረሱአትም ተቀመጡባትም። እግዚአብሔርም ለአባቶቻቸው እንደ ማለላቸው በዙሪያቸው ካሉት አሳረፋቸው፤ ከጠላቶቻቸውም መካከል ይቋቋማቸው ዘንድ የቻለም አልነበረም። ማንም ሰው አልቻለም። እግዚአብሔርም ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም (ኢያሱ 21:43-45)።

ይህ እውነት ለዛሬ ስንቃችን ነውና ዝም ብለን እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል እያሰላሰልን እርሱን ሳንጠረጥር በተስፋ ለመጠበቅ ልባችንን እናዘጋጅ። ጌታ ቃሉን እንደማያጥፍና አደራም እንደማይበላ ተገንዝበን ተስፋ እናድርገው።

<u>መዝሙር</u>፦ ቃሉን ከቶ የማያጥፍ

ታማኝ አምላክ ነውና፣

የነገረንን ሁሉ ፈጽሞ አይተናልና፣

ከፍ ከፍ እናድርገዋለን በምሥጋና ።

ቃል ኪዳን

ድሮ ድሮ ልብስ የሚታጠበው ወንዝ ተወርዶ እንዶድ እየተጨቀጨቀና ከልብሱ ጋር ተቀላቅሎ ወራጅ ውኃ ባጸዳው ዐለት ላይ በእግር እየተረገጠና በእጅ እየታሸ ነበር። ዕድሜ ለሥልጣኔ፣ ወንዝ ተወርዶ በውኃ የሚታጠብ ሳይሆን በማሽን የሚጸዳ ልብስ መጣ። ከተሜ ተሽቀርቅሮ የሚታይበት ሱፍ ወንዝ ወርዶ ቢታጠብ ሱሪው ቁምጣ፣ ኮቱም ከረጢት ይሆን ነበር።

ታዲያ አንድ ቀን አባቴ ልብሱን በማሽን ለሚያጥቡ ሰዎች እንድሰጥ አዘዘኝ። ልጅ ነኝና ታዘዝኩ። ልብሱ ከአጣቢው ቤት የመውጫው ቀን ሲደርስ ግን የማውጫ ቲኬቱ ጠፋብኝ። አጣቢዎቹ ደግሞ ቲኬቱን አይተው ከራሳቸው ቀሪ ጋር ካላገናዘቡ ልብሱን አይሰጡም። አባቴ እንዳይቀጣኝ ፈርቼ ያለ ቲኬት ይሰጡኝ ዘንድ ብለማመጣቸውም ወይ ፍንክች አሉና ጨከኑብኝ። አባቴን ግን የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠርኩ ልብሱን ላለማውጣቴ ሰበቤን አበዛሁና አሳመንኩት። አንድ ቀን ግን ቢጨንቀኝ ኪሱ ውስጥ የነበሩትን መታወቂያዎች ሰብስቤ ወደ አጣቢዎቹ በመሄድ ብለምናቸውም ከዓለት ጋር መታገል ሆነብኝ። ዕድሜ ልኬን ከምሳቀቅ ብዬ ለአባቴ የቲኬቱን መጥፋት ነገርኩት። እርሱም ችግር የለም በማለት በነጋታው አብረን ወደ ልብስ ቤቱ በመሄድ ልብሱ የእርሱ እንደ ሆነ ገልጾ እንዲሰጡት ጠየቃቸው። እነርሱም፣ «መታወቂያ አለምት?» ብለው ጠየቁት። ኪሱን ፈተሸና «የለኝም፣» አላቸው። ለካስ ሌላ ኮት ውስጥ ጨምሬው ኖሯል። እነርሱም፣ «ምን ነው ልጅዎ ትናንትና ይዞ መጥቶ አልነበር እንዴ?» ቢሉት፣ ወደ እኔ ዞሮ በጥፊ አላጋኝ። ማታ ደግሞ ራቁቴን ደም በደም እስክሆን ድረስ አድርጐ በአለንጋ ገረፈኝ። እጅቼ ሰንበር አውጥተው አበጡ። ለማጠፍ በምሞክርበት ጊዜ ጥዝጣዜው ሞትን ያስመርጥ ነበር።

ምንም እንኳ በእኔ ላይ የደረሰው ግርፋት ክርስቶስ ለሰው ዘር ሲል ከተቀበለው ሥቃይ ጋር ባይቀራረብም፣ የግርፋትን ሰቀቀን ግን በጥቂቱም ቢሆን እገነዘበው ዘንድ ረድቶኛል። አባቴ የመሰለውን (የለመደውን ማለት ይቀላል) ያደረገው እኔ በማጥፋቴ ነው። ክርስቶስ ኢየሱስ ግን ለግርፋትና ለሞት የሚያደርስ ምንም

ጥፋት አላጠፋም፣ አንዲት ስሕተት እንኳን አልፈጸመም። ማንም በፊቱ ቆሞ ስለ ኃጢአትና መተላለፍ ሊከስሰው፣ ሊወቅሰው ወይም ፋይል ይከፍትበት ዘንድ አይችልም። በነገር ሁሉ ተፈትኖ ንጹሕ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን፣ የእኛ ኃጢአትና በደል በእርሱ ላይ ሆነና ቅጣትን አመጣበት። እየተፈራረቁ በጅራፍ ገረፉት፣ ደም በጀርባው ላይ እንደ ሻወር ውኃ እየወረደ፣ ፊቱ ተጉረብርቦ፣ እጆቹ የፊጥኝ ተጠምዝዘውና ታስረው፣ ጥፊ ፊቱ ላይ ሲፈራረቅበት ዝም አለ። እንደሚታረድ በግ ተነዳና ይባሱኑ ታረደ። አሥራ ስምንት ቁጥር ምስማር እጆቹን ዘንጥለው አልፈው ከግንድ ጋር አጣበቁት፣ እጆቹም ሰውነቱን መሸከም ስለማይችሉ ምስማሩ እየዘነጠላቸው የእጁን ስንጥቅ አሰፉት። እግሮቹም በተራቸው ምስማር ዘልቆባቸው ደምን እያንጠባጠቡ አካሉን መሸከም ስለማይችሉ እነርሱም በምስማሩ ሹለት እየተዘነጠሉ ሥቃዩን አበዙት።

በጥይት ተመትቶ በአንድ ጊዜ ጸጥ ማለት እኮ እረፍት ነው። ዓይን እያየ ገላ ሲበሳ፣ ደም ሥሮች በምስማር ሲቆረጡ የሚኖረውን ሕመም አስቡት፣ እርሱ ግን በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ዝም አለ። ሐኪም ቤት መርፌ ለመወጋት ለያዥ ለገናዥ የምናስቸግር፣ ምስማር ቢመጣማ ነፍሳችን በአፍንጫችን ትወጣለች። እስኪ ዛሬ ሁሉም ይቅርና የጌታን የፍቅር ስፋት ጥልቀትና ርዝመት እያሰብን የሚቀጥሉትን ጥቅሶች እናስላስል፡- ማቴ. 27፡27-44፤ ማር. 15፡16-32፤ ሉቃስ 23፡26-31፤ ዮሐ. 19፡1-7።

<u>መዝሙር</u>፡- <u>ደሙ እንደ ውኃ</u> (2) ጐረፈ፣
የጌታ ጀርባ በጅራፍ ተገረፈ።
እግሩ እስኪነቃ ተራራውን ነጐደ፣
እስከ ሞት ድረስ ጌታ እኔን ወደደ።

«በሰፈሩት ቁና . . . »

ባለፈው ጊዜ፣ ጳውሎስ ፈቃዱ ከተባለ ተርጓሚ እንዲሁም የቀንዲል መጽሔት አዘጋጅ ከሆነው ከደረጀ በላይነህ ጋር «የጸጋው ብርታት» ስለሚል መጽሐፍ እንነጋገር ነበር። ይህ መጽሐፍ ጳውሎስ ተርጉሞት ደረጀና እኔ ደግሞ እርማት ቢጤ ሠርተን ነበር። ደረጀና ጳውሎስ፣ «እኛን የነካን የያዕቆብ ሕይወት ነው» አሉኝ። እኔ ደግሞ ሁለንተናዬን ሁሌ የሚንጠውና ልቤን የሚያጸናው የአብርሃም ታሪክ ስለ ነበር፣ የነካኝ የአብርሃም ታሪክ ነበር። «እናንተ ያዕቆብን የምትወዱት ታሪኩም የሚነካችሁ አጭበርባሪዎች ስለ ነበራችሁ ነው» ብያቸው ነበር።

ያዕቆብ እሳት የላሰ <ጩልሌ> ነው። እግዚአብሔር ምኑን አይቶ ይህንን አታላይ እንደ ወደደ የሚያስብ ሁሉ ይገረማል። ቤት ለቤት እየዋለ የወንድሙን ብኩርና በምስር ወጥ የነጠቀ፣ ከእናቱም ጋር ተስማምቶ አባቱን የሸወደ <መልቲ> ነው።

እግዚአብሔር ደግሞ ጥሎበት ድብን ያለ ፍቅር የያዘው፣ ከዚሁ <መናጢ> ጋር ነው። ሳያቀና ላይተወው ቃልን ሰጠው፣ «የነገርኩህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና፣» አለው። ከአባቱ ቤት ሸሽቶ በኃጢአት ተውጦ ሲቅበዘበዝ፣ ተስፋ በሌለበትና እግዚአብሔር ያለ በማይመስልበት ስፍራ በራእይ ተገልጦ ተንጠራርቶ ሊደርስበት የማይችለውን ሰማያዊ ምሥጢር ገለጠለት። ለጊዜው አጐቱ ቤት ቢጠለልም፣ ሰበባ ሰበብ እየፈለገ ለሃያ ዓመታት «አሸው»። ለአታላይ አታላይ ያዝለታልና፣ ለልያ ሰባት ዓመት፣ ለራሔል ደግሞ ሌላ ሰባት ዓመት፣ ምንዳውን እየቀያየረ ደግሞ ለስድስት ዓመት አንከራተተው። በብልጥነቱ ተማምኖ የእናቱን ምክር በመስማቱ፣ እግዚአብሔር ላባን አዘዘለት። እናቱም ርብቃ ዳግመኛ ልጇን ሳታየው ሞተች።

እግዚአብሔር አያይም ብለን ለምናደርገው ነገር መጠንቀቅ አለብን። በጨለማ ያለውን ወደ ብርሃን የሚያወጣ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው ይሰጥ ዘንድ ሁሉን የሚያይ አምላክ በሰማይ አለና እንዴት እንድንኖር እንጠንቀቅ። በቅጣት ውስጥ አልፈን ይህንን እውነት እንደ አዲስ ከመረዳት፣ አስቀድመን በማወቅና በማመን

እንዲሁም በመኖር እናሸንፈው። ጌታ በዘጉልቁ መጽሐፍ ውስጥ ሲናገር፤ «ኃጢአታችሁም እንዲያገኛችሁ እወቁ።» (32:23) ይላል። እግዚአብሔር ግን ይህንን አታላይ በፍቅሩ ገመድ ስቦ የያዕቆብ አምላክ ነኝ እያለ እስከ ዛሬ ይናገራል። ምንም እንኳን ያዕቆብ ስሙ ተሰውጦ እስራኤል ቢባልም፣ እግዚአብሔር ግን የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ ይላል። የያዕቆብ አታላይነቱ ከላዩ ላይ እስኪረግፍ ድረስ ዓመታት አልፈዋል። ዛሬም እንደ ያዕቆብ ከሰው ተሰውረን በሥጋ ብልጠት እግዚአብሔርን ማታለል የምንችል የመሰለን ብንኖር እንመለስ። ጌታም የኃጢአት ሥርን ከሕይወታችን አጥፍቶ ይታደገን ዘንድ እንማጸነው። ካልሆነማ . . .

<u>መዝሙር</u>፡- የጭኔ ሽሉዳ ተነክቶ አነክሳለሁ፣
ሊነጋ እስኪያቅላላ ከአምላክ ታግያለሁ።
ሰውነቴ ድኖ ቀረ፣
ስሜ እስራኤል ሆነ ተቀየረ።

በክርስቶስ አሸነፊ ከሆንን፣ መንፈሳዊ ውጊያ ትርጉሙ ምንድን ነው?

«በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ»
(ኤፌ. 6:10-18)::

ብዙ ጊዜ ግራ ከሚያጋቡኝ ስብከቶችና ለማስተማርም ብቃት ከሌለኝ ርእሶች መካከል አንዱ መንፈሳዊ ውጊያ ነው:: ውጊያው በጌታ ኢየሱስና በክፉው መካከል ተደርጐ በጌታ አሸናፊነት ከተጠናቀቀ እኛ ውጊያ ውስጥ መግባታችን ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ድሉ የሚታወቅ ከሆነ፣ ውጊያው ምኑን ጦርነት ሆነው? ደግሞስ አሸንፈናል ብለን የተረታንበት ጉዳይ ብዛቱ ስንት ይሆን? አንዳንድ ጊዜ ውጊያው አልቋል የእኛ ሥራ ደግሞ ዝም ብሎ ጌታ ሲሠራ ማየት ነው እንላለን:: ይሄ ነገር ግራ ያጋባናል::

ከነበረኝ ያለማወቅ ችግር በጥቂቱም ቢሆን ዓይኔን የከፈተልኝ በአንድ ወቅት በአሜሪካን ኤምባሲ ያጋጠመኝ ጉዳይ ነው:: ሰው ሁሉ አሜሪካ መሄድ ይፈልጋል:: ግን መሄድ አይችልም:: ለረጅም ጊዜ በተደጋጋሚ ተስፋ ባለመቁረጥ የቪዛ ጥያቄ የሚያቀርቡ ነገር ግን ቪዛ ያልተሰጣቸው ብዙ ወገኖች አሉ:: ለምን? ብሎ መጠየቁ መልስ የለውምና ዝም ብሎ መዝለሉ ይመረጣል:: ቪዛውን ለማመልከት ስገባ ማሟላት የሚገባኝን ነገር በተሰጠኝ ወረቀት ላይ አነበብኩት:: የተባልኩትን በሙሉ አዘጋጅቼ ስጨርስ ኤምባሲው ለእኔ ቪዛ ላለመስጠት የሚያስችል ምንም ምክንያት እንደሌለው ተረዳሁ:: ገና የቀጠሮ ቀኑ ከመድረሱ በፊት ቪዛውን እንደማገኝ እርግጠኛ ነበርኩ::

መንፈሳዊ ውጊያው ብመጠኑ ከላይ ከዘረዘርኩት አሳብ ጋር የሚገናኝ እውነታ አለው:: ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እየኖረ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ከሆነ፣ በመንገዱ በጌታ ድልን እንደሚቀዳጅ ቃሉ ይነግረናል:: እስኪ ዛሬ ቆም ብለን እስከ ዛሬ ውጊያ ብለን የፈረጅናቸውን፣ አሁን እየተጋፈጥነው ያለውንና ወደ ፊት ሊያጋጥሙን ይችላሉ ብለን ስለምናስባቸው መንፈሳዊ

ውጊያዎች እንጸልይ። በጌታ ፈቃድ ውስጥ ኖረን እንደ ፈቃዱም እየተመላለስን ለእርሱ ክብር ለመኖር እንትጋ።

<u>መዝሙር</u>፦ ንቁ ንቁ በሃይማኖት ጽኑ ጐልምሱ ጠንክሩ፤

መወለዱ አይደለም ዳግም መፈጠሩ፤

ከማደጉ ላይ ነው ዋናው ቁም ነገሩ።

ከንቱ ሩጫ

«ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው፤ ዋኖች ግን መሰለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው።» (ገላትያ 2፡2)

አምባሰል አውራጃ በአምባሰል ወረዳ ዳልባ ጊዮርጊስ በሚባል ስፍራ በአንደኛ ደረጃ መምህርነት ለአንድ ዓመት አገልግያለሁ። የእግር መንገዱ አድካሚና አሰልቺ መሆኑ ሳያንሰው፣ በጊዜው የነበረው ርእሰ መምህር ደግሞ የበኩሉን ያዋክበዋል። ተቆጣጣሪ ይመጣል ሲሉት፣ እኛም ሠርተን የማናውቀውን የትምህርት ዕቅድ ደብተር ላይ እያሰመርን እንለቀልቃለን። ታዲያ ተቆጣጣሪው (ሱፐርቫይዘሩ) መጥቶ ሲገመግመን ስሕተት እንዳያገኝ በቻልነው መጠን እንጠነቀቃለን፣ ተማሪዎቻችንም አላስፈላጊ ጥያቄ እንዳይጠይቁ ቅድሚያ የማስፈራሪያ ዲስኩር ቢጤ ይሰጣቸዋል። ሱፐርቫይዘሩ ሲሄድ ሁሉም ይቀርና ሲያሻው አንድ ሳምንት ተምሮ አንድ ወር ደግሞ የሚቀረውን የገጠር ተማሪ እንደየአመጣጡ እናስተምራለን። ቆም ብለን ራሳችንን ለመፈተሽ ፈቃደኞች አልነበርንም።

ከላይ ባነበብነው ጥቅስ ውስጥ እንዳየነው፣ ጳውሎስ የቱንም ያህል የተሳካ አገልግሎት ቢኖረውም፣ የቀደመ አገልግሎቱን ለማስፈተሽ ፈቃደኛ ነበር። በተለይ በጌታ ቤት የቆይታችን ዘመን ሲጨምር፣ ታዋቂነታችን ሲገንና ከታዋቂ አገልጋዮች ጋር ስንወዳጅ፣ ራሳችንን ወደ ላይ ስለምንሰቅል፣ ሥራችንን ቆም ብለን ለመመዘን እንቸገራለን። ነገር ግን በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፎ ብዙ ፍሬ ያየው ወንድማችን ጳውሎስ በከንቱ እንዳልሮጥ ብሎ ከሰጋ፣ እኛማ እንዴታ? ዓመት ሙሉ አጠራቅሞ ጳጉሜ ስትመጣ የአምስት ቀን «ፍልሰታ» ከመጾም፣ በየዕለቱ መንገዳችንን ብንመዝን ከኪሣራ እንድናለንና፣ ቆም ብለን ሕይወታችንን፣ ኑሮአችንንና አገልግሎታችንን እንመርምር።

እስኪ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አሰላስሏቸው

1. ጌታን ከማግኘቴ በፊት ኑሮዬ እንዴት ነበር?
2. እርሱን ካወቅሁት ስንት ጊዜ አለፈ?
3. እስከ አሁን ምን በጎ ነገር ሠራሁ? ምንስ አጠፋሁ?
4. ጥፋቴን እንዳልደግም ምን ባደርግ ይሻለኛል?

<u>መዝሙር</u>:- አገልጋይ ተብዬ በቤትህ ስጠራ
ለስምህ ስዘምር ሳወራ፣
ክብርህን ሰራሲ ወስጄ እንዳልገኝ፣
ጌታ ሆይ ጠብቀኝ፣ ጌታ ሆይ ጠብቀኝ።

የጦሳ ተራራ

ጦሳ ተራራ የሚገኘው በደሴ ከተማ ነው። በአንድ ወቅት ከአንድ ወንድም ጋር ከአገልግሎት ስንመለስ ደሴ አረፍን። ከተማው ውስጥ የገባነው ምሳ ሰዓት አካባቢ ስለ ነበር፣ ትንሽ አረፍንና አመሻሹ ላይ ወደ ዋድላ ደላንታ በሚወስደው ኮረኮንች መንገድ ስናቀና አብሮኝ የነበረው ወንድም፣ «ጦሳ ተራራ ላይ እንውጣ» አለኝ። «አይ፣ መሽቷል» አልኩት። እርሱም፣ «ግድ የለም፣» ብሎ መለሰልኝ። እኔም ቀበል አደረግሁና፣ «በዚህ ጨለማ ይህን ተራራ መውጣት ያለ ክርስቶስ የምንኖረውን ኑሮ ይወክላል፣ መከራ ነው» ስለው፣ እርሱም መልሶ፣ «አይ መሐሪ፣ ያለ ክርስቶስ የምንኖረው ወደ ላይ መውጣት ሳይሆን በድቅድቅ ጨለማ ከተራራው ጫፍ ወደ ታች እንደ መውረድ ነው።» አለኝ። ስቅጥጥ አለኝ።

እስኪ አስቡት የዓይንን ብሌን ቢወጉት በማያሳይ ድቅድቅ ጨለማ ከተራራ ቁልቁል ስትወርዱ፣ ጌታ ግን ሲናገር እንዲህ ብሏል፣ «በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።» (ዮሐ. 12:46)። የጊዜ ርዝመት የነበርንበትን ጨለማ ያስረሳን ብንኖር፣ ውለታ ዘንጊዎች እንዳንሆን እንደገና መለስ ብለን ከምን ዓይነት ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን እንደ መጣን በማሰላሰል ለዚህ ያበቃንን ጌታ ስሙን እናወድሰው። ጌታ ኢየሱስን በማመናችን ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብለን የነበርንበትን ሁኔታ እናስብ፣ ተስፋ ቢስነታችንን፣ መቅበዝበዛችንን፣ ግራ መጋባታችንንና እረፍት ማጣታችንን ለውጦ ተስፋን ሰጠን። ልባችንን መለሰልን፣ የሕይወትን ትርጉም እንድንረዳ የልቦናችንን ዓይኖች በመክፈት ከአእምሮ በላይ የሚያልፍን ሰላምና እረፍትን ሰጠን።

እኛን ለዚህ ያበቃንን ጌታ ሌሎችም አውቀውት አርነት እንዲወጡ የተለማመድነውን ሰላም፣ የቀመስነውን እረፍት፣ ያየነውን ደግነቱን እንንገራቸው።

መዝሙር፡- ኑሮ ያለ ጌታ ታክቶኝ፣
ኃጢአቴም አስመርሮኝ፣
ወደ ኢየሱሴ ብመለስ የእርሱ ደግነት ማርኮኝ፤
በድል ጮዳና ብገባ ፍቅሩ ነፍሴን ቢገዛ፣
ጉልበቴን ለጠላት ላልሰጥ ቃል ገባሁኝ ለጌታ።።

የትራፊክ ቅጣት

ምልክት በሌለበት ቦታ ላይ፣ «ድሮ ነበረ፣ አሁን መኪና ገጭቶት ተነሥቶ ነው።» ብለው የቅጣት ቲኬት የሚሰጡ ትራፊክ ፖሊሶች አጋጥመውኛል። መንጃ ፈቃድ ስናወጣ ብዙ ምልክቶችን አጥንተናል። በተቻለን መጠን ሕጉን ማክበር ይጠበቅብናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የመንገዱን ሁኔታ የሚገልጡ፣ የሚያስጠነቅቁና የሚከለክሉ ምልክቶች ያስፈልጉናል። ምክንያቱም ምልክት ከሌለበት መተላለፋችንን አናውቅምና ነው። በመሆኑም፣ ምልክት ባለበት ቅጣት ሲቀጡን ማጉረምረማችን አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገርም፣ ሕግ ከሌለ ሰው መተላለፍን አያውቅም ይላል። ኃጢአት የሚታወቀው በሕግ ነው (ሮሜ 3:20)። ሕግ በሌለበት ደግሞ መተላለፍ የለም (ሮሜ 4:15)። ምንም እንኳን ጽድቅ በክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል የተሰጠ ነፃ ስጦታ ቢሆንም፣ እምነት በበጎ ሥራ ይገለጣል። ያኔ ሕግ በእምነት ይጸናል። ለመዳን ሳይሆን ስለ ዳንን ሕግን እንጠብቃለን። ሕግ በሌለበት ኃጢአት አይቆጠርም፣ ሕግ ባለበት ግን መተላለፋችንን እናውቃለን። በክርስቶስ ሞት ታርቀን የፈሰሰው ደሙ ቁጣውን ስላራቀልን እንደ አዲሱ ማንነታችን ለጌታ የተገባ ኑሮን ኖረን ለማለፍም እንተጋለን።

በመሠረቱ የትራፊክን ሕግ የምንጠብቀው የቅጣት ቲኬት ፈርተን ሳይሆን፣ በሰዎችና በንብረት ላይ አደጋ እንዳናደርስ አስበን መሆን አለበት። ነገር ግን ሕግ አስከባሪዎች በአግባቡ ስላልቀጡን፣ እኛም አዩን አላዩን እያልን በመሸማቀቅ እናሽከረክራለን።

እግዚአብሔር ጉዕ ፈልጐ ሰዎችን አይቀጣም፣ ወይ ደግሞ ሰበብ ፈልጐ ሰዎች ያሸረግዱለት ዘንድ አያስጨንቅም። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንድንጠብቃቸው የታዘዝናቸው ትእዛዛት ቢኖሩም፣ የምንጠብቃቸው ሁልጊዜ ቅጣትን በመፍራት ሳይሆን ሳንፈጽማቸው ብንቀር የምናደርሰውን ጉዳት አስበን ቢሆን መልካም ነው። ነገር ግን ድንበር ጥሶ የሚሄድ መቀጣቱ አይቀሬ ነው። እስከ

ዛሬ ድብብቆሽ ከእግዚአብሔር ጋር የምንጫወት ብንኖር እንኳን ጨክነን ከዐመፅ እንራቅ፣ መዋሸት እናቁም፣ ሐሜት ያብቃ፣ ስርቆት ይቅር፣ ሽንገላም ከእኛ ይራቅ።

<u>መዝሙር</u>፦ ራሴን ልመልከተው አጥርቼ፣ ሌላውን ትቼ፣
ዓይኔን ወደ አንተ መልሰው፣ ምናለኝ ከሰው።

እግዚአብሔርን መፍራት ዘመንን ታረዝማለች

(ምሳሌ 10:27)

አንዳንድ ሰው መኖር እየፈለገ ይሞታል። ሌላው ደግሞ መኖርን ጠልቶና ተንገሽግሾ ሞትን እየተመኘ ግን ይኖራል። ጤነኛ ነው ብለን ረጅም ዕድሜ የተመኘንለት ሰው ቶሎ ይሞታል። ለሞት አምስት ጉዳይ ናቸው ያልናቸው አሮጊቶች ደግሞ ከቀን ወደ ቀን እያማረባቸው ይኖራሉ። የተመኙትን ሁሉ አግኝቶ ለአጭር ዘመን ተንፈላስሶ መሞት ይሻላል፣ ወይስ እንዲያው በጀም ከፋም ረጅም ዕድሜ ኖሮ ማለፍ? ሁለቱም ያጓጓሉ። ቢቻልማ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ሆኖልን፣ ደግሞም ረጅም ዕድሜ ብንኖር እንመርጣለን።

ከላይ ያነበብነው ጥቅስ ዘመንን ለማርዘም እግዚአብሔርን መፍራት ያዋጣል ይለናል። ይህ ማለት ግን ፈሪሐ እግዚአብሔር እያላቸው በወጣትነታቸው ያሸለቡትን እንደ ተቀሰፉ አያስቆጥረንም፣ ወይም ኃጢአትን እንደ ጀብዱ እየተጉበት ክህደትን እያወጁ ዘመናቸው የረዘመ በጽድቃቸው እንደ ኖሩ አያሳይም። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ከሆነ አገሩን ይወድዳል፣ ወገኑን ይወድዳል፣ ቤተሰቡን ያፈቅራል፣ ሥራውን ያከብራል፣ ከክፉ መንገድና ከዐመፅ ጉዳና እንዲሁም ከኃጢአት ጽዋ ይርቃል፤ አእምሮው ሰክኖ ልብ ገዝቶ ይኖራል። በዝሙት ከሚመጣ ተላላፊ በሽታ፣ ከጠብና ክርክር፣ እንዲሁም ከግርግር ራሱን በማግለል መልካም ነገር ያለበትን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ነገር ይመርጣል። ልብ ገዝቷልና የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ተግባራዊ ያደርጋል። በዚህም ካላስፈላጊ ሞት፣ በሽታና ሥቃይ ይድናል። ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ቢፈራ፣ ከራሱ ይልቅ ለሌሎች በጐ ነገር ይመኛል። በቅናት መገዳደል፣ መሰራረቅ እንዲሁም ለራሳችን ጥቅም ስንል የምንፈጽማቸውን ክፋቶች እናቆማለንና በአላስፈላጊ ሁኔታ በአጭሩ የሚቀጨው የሰው ሕይወት ይረዝማል።

ብዙ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት በማመናችን ያገኘነውን እረፍትና ሀብት በዘመን ርዝመት እንዘነጋዋልን። በጌታ ስንሆን ያገኘነው የዘላለም ሕይወት ብቻ ሳይሆን በምድርም ረዥም ዕድሜን

ነው። ከዐመፅ በመራቅ ዕድሜያችንን ሊያሳጥር የተሰለፈውን ክፋት አምልጠን፣ መልካም ዘመንን አሳልፈን ከሕይወት ወደ ሕይወት እንሻገራለን። እስኪ ዛሬ ጌታን ከክፋት ሰውሮና ከሞት አስመልጦ ዘመናችሁን ስላረዘመው አመስግኑት። የምስጋና መዝሙር መርጣችሁ ቢያንስ በቀን ውስጥ ሦስት ጊዜ በዝማሬ አክብሩት።

<u>መዝሙር</u> :- ክርስትናዬ ጠቀመኝ (2X)

ውሎ እያደረ ጣፈጠኝ።

ከእግዚአብሔር ጋር ተጓዳኝ፣

ቢያገኝም ቢያጣም አመስጋኝ፣

ቢወድቅም እንኳን ይነሣል፣

ምርኩው ይመለሳል።

«አሚማቴን አሳምርልኝ»

2ኛ ዜና 16:11-14

በደርግ ዘመን ዓሊ ሙሣ የሚባል የወሎ አስተዳዳሪ ነበር። ይህ ሰው እምብዛም የተማረ አልነበረምና ሰው ለመግደል አይፈራም ነበር። ከዚህ የተነሣ ሰዎች ስሙን ሲሰሙ እንኳ ይንቀጠቀጣሉ። ታዲያ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት «ወያኔዎች» አዲስ አበባ ሲገቡ ጐጃም መንገድ፣ ሰሜን ሆቴል አካባቢ ራሱን ገድሎ ተገኘ። በተዋጊነቱ ለአእምሮ በሚከብድ የውጊያ ድፍረቱ የሚታወቀው ኃየሎም አርአያም አንድ ቡና ቤት ውስጥ በአንድ ጐልማሳ ተገደለ። ዓለም ያደነቃቸው ንጉሥ ኃይለ ሥላሴም ቢሆኑ የማታ ማታ አድሃሪ ተብለው በትራስ ታፍነው ተገደሉ። በለማላጋ ቁመቷ፣ ውበቷና ቸርነቷ የምትታወቀው ልዕልት ዲያናም ጋዜጠኛ ሽሽታ ስትከንፍ ቀኗ ተቆርጦ ኖሮ በመኪና አደጋ ምክንያት እስከወዲያኛው አሸለበች።

አሳ የተባለውም የእስራኤል ንጉሥ አባቱ አብያ ሲሞት በምትኩ ነገሠ (2ኛ ዜና 14)። በዘመኑም፦

> *«ምድሪቱ አሥር ዓመት ያህል ዐረፈች። አሳም በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን ነገር አደረገ፤ የእንግዶቹንም አማልክት መሠዊያ የኮረብታውንም መስገጃዎች አፈረሰ፣ ሐውልቶቹንም ሰበረ፣ የማምለኪያ ዐፀዶቹንም ቆረጠ . . .» (ቁ.1-8)።*

ከዚህም የተነሣ መንግሥቱ ጸና፣ ምድሪቱም ዐረፈች፣ ጠላቶቻቸውን ሁሉ ረቱ። እናቱ የማምለኪያ ዐፀድን ጣዖት ብታደርግ፣ እቴጌነቷን ገፍፎ አዋረዳት። የአሳ ልብ በዘመኑ ሁሉ (ለ35 ዓመታት) ፍጹም ነበር። የኋላ ኋላ ግን በሠላሣ ስድስተኛው ዓመት በሦርያ ንጉሥ ታመነ። በሠላሳ ዘጠነኛውም ዓመት አሳ እግሩን ታመመ፣ ደዌውም ጸናበት፣ ለፈውሱም እግዚአብሔርን ሳይሆን ባለ መድኃኒቶችን ፈለገ። በነገሠ በአርባ አንደኛውም ዓመት ሞተ።

ይህን ታሪክ ሳስብ ሁልጊዜ ጌታ ሆይ፣ አሚሚቴን አሳምርልኝ

እላለሁ። እናንተም እንዲሁ እንደምትሉ አምናለሁ። ከጌታ ጋር እንደ ጀመርነው እንዲሁ እየተጋን ይሆን፣ ወይንስ መንገድ ስተናል? የጌታ መምጫ እየተቃረበ ጊዜው ሲመሽ፣ እኛስ ከጀመርንበት የት ላይ ደርሰን እንገኝ ይሆን? የዘመን ርዝመት ክርስትናችንን ወግ ብቻ አድርጐብን፣ እኛም እንደ ሌሎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሌላ ነገር ታምነን ይሆን? ዛሬ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከጌታ ጋር እየተነጋገርን እንዋል። ከላይ ያነበብነውን ታሪክ በሙላት ከዜና መዋዕል ካልዕ 14 ጀምረን እያነበብን፣ ጌታም ፍጻሜያችንን እንዲያሳምር እንጸልይ።

መዝሙር፦ ቀርቶብኝ ጥቅሜ ሁሉም ነገር፣
ልኑር ዘለዓለም ጌታ ካንተ ጋር፣
መምጫህ ሲቃረብ ጊዜው ሲመሽ፣
ተስፋ ቆርጬ ካንተ እንዳልሸሽ።

ኢዮርብዓም- የትውልድ ነቀርሳ

የመጀመሪያዋ ልጁ ጤነኛ ነበረች። የኋላ ኋላ ግን እየተደበቀች ማድረግ የፈለገችውን ሁሉ ፈጸመች። ወንዶችን እንደ ዳቦ ቤት ወረፋ ደርድራ አፈራረቀች። መጠጥ እንደ ውኃ፣ የሲጃራ ጢስ እንደ ባቡር እያቦነነች ያሻትውን አደረገች። ታናሽ ወንድሟም ፈለጓን ተከተለ፤ ትምህርቱን አቋርጦ መረን ወጣ። የእርሱ ታናሽ ደግሞ ትንሽ አፈንግጣ በዚያው ፈርጥጣ ሴተኛ አዳሪ ሆነች። የቀሩት ሁለቱም የበላዮቻቸውን ተከትለው ገና በልጅነት «ካብ አይገባ ድንጋይ» ሆኑ።

የመጀመሪያዋ ተጣመመች፣ የቀሩትም መንገዷን ተከትለው ጭራሽ የባሱ ሆኑ። ምንም እንኳ ሰው ለራሱ ክፋት ራሱ ተጠያቂ ቢሆንም፣ ለጥፋት ምሳሌ የሆነው ደግሞ የበለጠ ይቀጣል።

የኢዮርብዓም ታሪክ እንዲሁ ነው። ምንም እንኳን ከእርሱ በፊት ያጠፉም ያለሙም ቢኖሩም፣ እርሱ ግን የክፋት መንገድ በር ከፋች ሆኖ ከእርሱ በኋላ ለመጡት የጠማምነት ምሳሌ ሆነ። እርሱ ገርበብ አድርጐ የከፈተውን በር፣ ፈጣኑ ትውልድ ደግሞ ወለል አድርጐ በረገደው። እግዚአብሔርን መፍራት እንደ ቂልነት ተቆጥሮ፣ ለማይታወቁ ባዕድ ጣዖታት አምልኮ ይጐርፍ ጀመር። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ታሪክ የዘገቡት ጸሐፍት ደግሞ አንድ ንጉሥ ሲያጠፋ በኢዮርብዓም መንገድ እንደ ተጓዘ አድርገው ታሪክን እያጣቀሱ አስረዱ። ኢዮርብዓም የትውልድ ነቀርሳ ነው።

ዛሬ እኛ የክርስቶስ ማስታወቂያዎች ነን። ሰው ሁሉ ያነብበናል። መሪዎች ብንሆንም፣ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ ሰዎችን ወደ በጎ አለያም ደግሞ ወደ ከፋ ጎዳና የመምራት ኃላፊነት በእጃችን አለ። ምርጫው የራሳችን ነው። ዛሬ በእጃችን ያለው ትናንት የእኛ ያልነበረና ነገ ከእጃችን የሚወጣ በመሆኑ፣ ዛሬውኑ ለመልካም ነገር እንጠቀምበት። ለጸጸት የማይዳርግ ሕይወትን ኖረን ለማለፍ ኑሮአችን ምልክት መሆኑን አውቀን፣ እኛን የሚያዩን ሰዎች መኖራቸውን ተገንዝበን እንደሚገባ ለመኖር ራሳችንን እናዘጋጅ። የበጐ ነገር ምሳሌ እንሁን።

«. . . የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው።» (2ኛ

ቆሮ. 3:3)። እስኪ ዛሬ በትምህርት ቤት፣ በሥራ፣ በአገልግሎትና በተሰማራንበት መስክ ሁሉ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ለክርስቶስ መንገድን የሚጠርግ ሥራ ሠርተን እንዋል? ጌታ እንዲረዳንም እንጸልይ።

መዝሙር :- ልሆን አልፈልግም ግብዝ ፈሪሳዊ፣
በውስጤ ሳይኖረኝ ደርሶ መንፈሳዊ፤
ድርቀትንም አልወድ ብዙ መደካከም፣
በሆነ ባልሆነው ባንተ ማጉረምረም፤
ጌታዬ ሆይ፣ አደራ የምልህ፣
አሁን ባለኝ ሕይወት አጽናኝ ስለ ስምህ።